| | |
|---|---|
| ዐይነት ፤ | ርእስ ፡ አንቀጽ ። |
| ርእስ ፤ | *"በሥልጣኔ ፡ የተሠራ ፡ ሀገር ፡ በስይጣኔ ፡ አይፈርስም!"* |
| ደራሲ ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና" ፡ መዜንው ።* |
| ዕለት ፤ | *ሚያዝያ* ፡ 2017 ፡ ዓ.ም. ። |
| ዝግጅት ፤ | ፍጹም ። |
| መጽሔት ፤ | *"ሥልጡንሕዝብና"* ፥ ቍ.2017-003 |
| ማስታወሻ ፤ | |
| ማሳሰቢያ ፤ | |

# ርእስ ፡ አንቀጽ ።

editorial | éditorial | اِفْتِتاحي

## በሥልጣኔ ፡ የተሠራ ፡ ሀገር ፡ በስይጣኔ ፡ አይፈርስም!

### ከዓለም ፡ ሰላም ፡ ወደ ፡ ሣልስ ፡ የዓለም ፡ ጦርነት?




ኢትዮጵያ ፥ ሚያዝያ ፡ ፳፯ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፫ ፡ ዓ.ም. ፥ የኢጣልያ ፡ ፋሺዝምን ፡ እና ፡ በጠቅላላው ፡ የምዕራባውያንን ፡ ቅኝ-ገዢነት ፡ ድል ፡ ባደረገች ፡ ባ4 ፡ ዓመት ፡ ከ3 ፡ ቀኑ ፥ አውሮፓም ፡ ሚያዝያ ፡ ፴ ፡ ቀን ፡ ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ.ም. ፡ የጀርመንን ፡ ናዚዝም ፡ ድል ፡ አደረገች ። የኹለቱ ፡ ወገኖች ፡ ድል ፥ በስይጣኔ ፡ ላይ ፡ የተገኘ ፡ የሥልጣኔ ፡ ድል ፡ ተብሎ ፡ በዓለም ፡ ታሪክ ፡ ሲተረክ ፡ ይኖራል ።

ተመሳሳይ ፡ አደጋ ፡ በዓለም ፡ ላይ ፡ ለሦስተኛ ፡ ጊዜ ፡ እንዳይከሠት ፥ ዐዲስ ፡ አህጉራዊ ፡ ሥምረት ፡ (Charter) ፡ በድል ፡ አድራጊዎቹ ፡ መንግሥታት ፡ ተረቀ ፥ በዓለም ፡ ሐራ ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ ተፈርሞ ፥ የተባበሩት ፡ መንግሥታት ፡ ድርጅት ፡ ባ፲፱፻፴፯ ፡ ዓ.ም. ፡ በወግ ፡ ተመሠረተበት ።

በድል ፡ የተጠናቀቀው ፡ የኢትዮጵያ ፡ ፀረ-ቅኝ-ግዛት ፡ እና ፡ ፀረ-ፋሺዝም ፡ ተጋድሎ ፥ ከቬዬትናም ፡ እስከ ፡ ኧልጀዘኢር ፣ ከህንድ ፡ እስከ ፡ ጋና ፣ ከኢንዶኔዝያ ፡ እስከ ፡ ጃማይካ ፥ በቅኝ-ገዢዎች ፡ መንግሥታት ፡ ላይ ፡ ኀይለኛ ፡ የነጻነት ፡ ተጋድሎን ፡ ስለ ፡ ቀሰቀሰባቸው ፥ ኻያ ፡ ዓመት ፡ ባልሞላ ፡ ጊዜ ፡ ውስጥ ፡ አብዛኛዎቹ ፡ ቅኝ-ግዛቶች ፡ ሐራነትን ፡ አገኙ ።

ከዚያ ፡ ወዲህ ፥ *"ይህች ፡ ባቄላ ፡ ያደረች ፡ እንደኹ ፡ አትቈረጠምም"* ፡ ብለው ፥ ቅኝ-ገዢዎች ፡ መንግሥታት ፡ ኹሉ ፡ በኢትዮጵያ ፡ ላይ ፡ ቂም ፡ ያዙባት ። ፍርስቷን ፡ በስይጣኔ ፡ ዐቀዱባት ፤ ያቀዱባትንም ፡ በስይጣኔ ፡ ፈጸሙባት ። ዐመፀኞችን ፡ መልምለው ፥ በወንብድና ፡ አስሰማሩባት ። እነሶቬዬት ፡ ኅብረትን ፡ እና ፡ እነዩጎስላቬያን ፡ ያፈረሰውን ፡ ኪነ-ስዕረታቸውን ፡ ኹሉ ፡ በኢትዮጵያም ፡ ላይ ፡ አወረዱባት ። ኢትዮጵያ ፡ ተጐዳች ፤ ልጆቿ ፡ በጦርነት ፡ እና ፡ በረኃብ ፣ በስደት ፡ እና ፡ በበሽታ ፡ ዐለቁ ። የኢትዮጵያ ፡ ጩኸት ፡ ራማ ፡ ደረሰ ፤ መልስም ፡ እንሆ ፡ መጣላት ። ጠላቶቿ ፡ ዳግም ፡ ወደ ፡ ጦርነት ፡ ተሳቡ ። ኪሪአላይሶን! ጌታ ፡ ሆይ! ማረን ፨

እግዚእናችንን ፡ የማስከበር ፥
ሕገ ፡ መንግሥታችንን ፡ የመሥራት ፥
ሥልጡንሕዝባዊ ፡ የርትዕ ፡ መንግሥታችንን ፡ የማቆም ፡

ሀገራዊ ፡ ዐላማችንን ፡ ለመፈጸም ፥ በኢትዮጵያና ፡ በመላው ፡ ዓለም ፡ የምንገኝ ፡ ሀገራውያን ፡ ኢትዮጵያውያን ፥ ሕዝባዊ ፡ አንድነታዊ ፡ አካላችን ፡ ለኾነው ፡ **ለኢ.ሀ.ሥ.አ. ፡ እናብር!**

የኢትዮጵያውያን ፡ ሀገራዊ ፡ ሥልጡንሕዝባዊ ፡ አንድነት ።

# ሥልጡንሕዝብና ።

www.slttunhzb.net


©ኢ.ሀ.ሥ.አ. ፥ 2017 ፡ ዓ.ም. ።